**ተዛማጅ ምንጮች፡-** JEE-RA፣ KLA፣ KLA-RA
**ኃላፊ ጽ/ቤት፡-** ዋና የሥራ አስፈፃሚ/Chief Operating Officer

# ስለ ተማሪ ዝውውሮች

A. **ዓላማ**

የት/ቤት ምደባ ለውጥ (COSA) ተብሎ ስለሚጠራው ተማሪዎች ከአካባቢያቸው ት/ቤት ወይም ከግላዊ ሁኔታ የትምህርት ፕሮግራማቸው (IEP) ውጭ ወደ ሌላ ት/ቤት ዝውውር ሊሰጣቸው የሚችሉባቸውን ውስን ሁኔታዎችን ለማብራራት፡-

B. **ጉዳዩ**

ተማሪዎች በሚኖሩበት አካባቢ (የአካባቢ ት/ቤት) ወይም በ IEP ፕሮግራማቸው መሰረት በተመደበላቸው ት/ቤት እንዲከታተሉ ይጠበቅባቸዋል። ተማሪዎች በአካባቢያቸው ትምህርት ቤት ወይም በ IEP አሠራር በተመደቡበት የገጠማቸው ከባድ ሁኔታ ሲኖር፣ ቤተሰብ በቅርቡ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ ቦታ የቀየሩ ከሆነ፣ እና በአንዳንድ ሁኔታዎች ወንድም/እህት በሚማሩበት ትምህርት ቤት ለመማር አስፈላጊ ሲሆን ለ COSAs ማመልከቻ ማቅረብ ይችላሉ።

C. **ሁኔታ**

1. አንድ ተማሪ በማንኛዉም በሚከተሉት መስፈርቶች መሰረት ለ COSA ማመልከት ይችላል/ትላለች፡-

   a) ልዩ ችግር

      የትምህርት ቤት አካባቢ ለውጥ ቢደረግ ሁኔታቸው ማለትም አካላዊ፣ አእምሯዊ፣ ወይም ስሜታዊ ደህንነት ወይም ከቤተሰብ ግላዊ ሁኔታ ጋር የተዛመዱ የተባባሱ/የከፉ ሁኔታዎች ሊሻሻልላቸው የሚችል ከሆነ ተማሪዎች ለ COSA ማመልከት ይችላሉ። ሆኖም ግን ሌሎች አስገዳጅ ምክንያቶች ካልኖሩ በስተቀር፥ ለብዙ ቤተሰቦች የጋራ የሆኑ ችግሮች እንደ ልዩ ችግር አይታሰቡም። ሁሉም የከባድ ችግር ጥያቄዎች ለየብቻ ሊረጋገጥ የሚችል ሰነድ አባሪ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል፣ አለዚያ ጥያቄው ውድቅ ይደረጋል። እንደዚህ ያሉ የልዩ ችግር ምሳሌዎች፣ በዚህ የሚወሰኑ ባይሆንም የሚከተሉትን ያካትታል፡-

      (1) የልጅ እንክብካቤ/ጥበቃ

         ወላጆች/ሞግዚቶች ከትምህርት ቤት ሠዓት በፊት ወይም በኋላ ለተማሪዎች ዕድሜ የሚመጥን ቁጥጥር ማድረግ አለባቸው ምክንያቱም፡-

         (a) በአካባቢያቸው ትምህርት ቤት ዙርያ ለሚገኙ የልጅ እንክብካቤ ፕሮግራሞች እና እንቅስቃሴዎች የሥራ ሰዓታቸው ከመደበኛዉ ሰዓት በእጅጉ የሚያልፍ ወይም በሌላ መልኩ በቀላሉ ተደራሽ የሆነ የሕፃናት እንክብካቤ ፕሮግራም የማያገኙ ከሆነ፤ እና/ወይም

         (b) ቤተሰቡን ለሕፃናት እንክብካቤ ተደራሽነት የሚገድብ ጉልህ የሆነ የገንዘብ ችግር፣ ወይም በሌሎች የተለዩ የተማሪ ሁኔታዎች ምክንያት የሚከሰቱ

ፍላጎቶች። ከአንደኛ ደረጃ ባሻገር ላሉ ተማሪዎች ሁኔታዎቹ አስቸጋሪ እና እጅግ በጣም ወሳኝ/ትርጉም ያለዉ መሆን አለበት።

(2) የተማሪን አካላዊ፣ አእምሯዊ፣ ወይም ስሜታዊ ደህንነትን የሚመለከቱ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲኖሩ።

(a) በዚህ ምክንያት COSAs የሚፈልጉ ወላጆች/ሞግዚቶች ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው –

(i) ከት/ቤቱ ሁኔታ ጋር በቀጥታ የተዛመዱ ወይም በተማሪ አካላዊ፣ አእምሯዊ፣ ወይም ስሜታዊ ደህንነት ጋር የተዛመዱ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳደሩ በጤና እንክብካቤ ባለሙያ በመካሄድ ላይ ያሉ የሕክምና ጉዳዮች፤ እና/ወይም

(ii) ልዩ እንክብካቤ የሚሹ ከባድ የጤና ጉዳዮች (ለምሳሌ፡- ከልጁ/ከልጅቷ የአካባቢ ትምህርት ቤት እና/ወይም ከወላጅ/አሳዳጊ የስራ ቦታ ርቀው የሚገኙ ተደጋጋሚ የህክምና ቀጠሮዎች)።

እነዚህ ሰነዶች ከሌሉ፥ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን የሚያሳይ ማስረጃ ከት/ቤት ሰራተኞች ጋር በመነጋገር ማግኘት ይቻላል።

b) የቤተሰብ የአድራሻ ለዉጥ

ቤተሰባቸው በሞንትጎመሪ ካውንቲ ዉስጥ የመኖሪያ ቦታ ለውጥ ያደረጉ ተማሪዎች፣ በትምህርት አመቱ ዉስጥ ተማሪዎቻቸዉ በነበሩበት የአካባቢያቸዉ ት/ቤት ለመቀጠል ከፈለጉ ምንም የከባድ ችግር ምክንያት ሳያቀርቡ COSA ለመጠየቅ ይችላሉ። እንደዚህ አይነት ጥያቄዎች መቅረብ ያለባቸው ቤተሰብ አካባቢ እንደቀየረ ወዲያውኑ መሆን አለበት፥ እና ጥያቄዎቹ የሚፈቀዱት ለትምህርት ዓመቱ ቀሪ ጊዜ ብቻ ይሆናል፣ ቢሆንም የ11ኛ ወይም 12ኛ ክፍል ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እስከሚያጠናቅቁ ድረስ COSA እንዲቀጥሉ ሊፈቀድላቸው ይችላል።

c) እህት/ወንድም

(1) አንድ ተማሪ ትምህርት ቤት በሚጀምርበት-በምትጀምርበት ዓመት፣ ወንድም ወይም እህት ወዳሉበት መደበኛ/አጠቃላይ የትምህርት ቤት ፕሮግራም፣ ወይም ስፔሻል ትምህርት ፕሮግራም ለመግባት ሲፈልግ/ስትፈልግ

(2) ለአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ብቻ፥ ወንድም/እህት የማግኔት፣ የቋንቋ ኢ.መርዥን፣ ወይም ሌላ አፕሊኬሽን ፕሮግራም፣ የሚማሩ ከሆነ ለመደበኛ ትምህርት ቤት ፕሮግራም እንደ ጉዳዩ ሁኔታ እየታየ ለወንድም/ለእህት COSA ሊፈቀድ ይችላል

(3) እንዲህ አይነት ጥያቄዎችን ተቀብሎ መፍቀድ የሚቻለው በመማሪያ ክፍል ቦታ ከተገኘ፣ በክፍል ደረጃ የሠራተኞች ምደባ ከተሟላ፣ ወይም በሚያመለክቱበት ትምህርት ቤት ላይ ተጽእኖ የሚያስከትሉ ሌሎች ምክንያቶችን ጭምር ግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል።

(4) የድንበር ማካለል ለውጥ ከተከሰተ ከላይ የተዘረዘሩት ንኡስ ክፍል (1) (2) እና (3) አይተገበሩም።

(5) በዚህ ፖሊሲ አፈጻጸም መሠረት እህት/ወንድም ሲባል፥ ከእንጀራ እናት/አባት የተወለዱ (የደም ግንኙነት የሌለበት እህት እና ወንድም) እና ከአባት ወይም ከእናት የተወለዱትን (በእናት ወይም በአባት በአንዱ ወገን ብቻ የሚጋሩት እህት/ወንድም)ያጠቃልላል።

d) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች

(1) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ታይትል I ት/ቤቶችን (Title I Schools)፣ ኢኖቬቲቭ ስኩል ይር ካላንዳር ስኩልስ (Innovative School Year Calendar Schools)፣ ወይም ፎከስ ስኩልስ (Focus Schools) በማናቸውም በእነዚህ ት/ቤቶች የሚሠሩ ሠራተኞችን ለማበረታታት እና ድጋፍ ለመስጠት በተቀመጠው የስትራቴጂ ትኩረት መሠረት፥ የራሳቸው የሆኑ ልጆቻቸው በሚከተሉት ምክንያቶች እነርሱ በሚሠሩባቸው ትምህርት ቤቶች እንዲዛወሩ ለመጠየቅ ይችላሉ፡-

(a) ለመጪው የትምህርት ዓመት ከዚህ በላይ በተገለጹት ትምህርት ቤቶች በሙሉ ጊዜ ሠራተኛነት (FTE) የተመደበ(ች) እና የዓመት ፈቃድ፣ የጡረታ፣ እና የጤና ሽፋን ጥቅማጥቅሞች ያለው በጀት ተመድቦለ(ላ)ት የሚሠራ-የምትሠራ ሠራተኛ፥ እና

(b) የሥራ ባልደረባው(ዋ) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪ የሆነ(ች) እና ተማሪው(ዋ) ወደ MCPS ለመመዝገብ ብቁ የሚሆን-የምትሆን ከሆነ(ች)፣ እና

(c) ጥያቄው ከልጅ እንክብካቤ ጋር የተያያዘ ከሆነ ወይም ዘወትር የሥራ ባልደረባው(ዋ) ሥራ ላይ በሚሆንበት-በምትሆንበት ቀናች ተጨማሪ ክትትል የሚያስፈልግ ከሆነ።

(2) ሰራተኛዉ/ዋ በሚሠራበት/በምትሰራበት ትምህርት ቤት የተማሪው(ዋ) መመደብ ሰራተኛው(ዋ)ን አጥጋቢ በሆነ መንገድ የማከናወን ችሎታዉ(ዋ)ን የሚያደናቅፍ ከሆነ፣ የተማሪ ዝውውሩ እንደገና ሊታገድ ይችላል።

(3) የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት እንደዚህ ያሉ ጥያቄዎችን የማገናዘቢያ ሂደት እና የጊዜ ሰሌዳ ላይ በመመስረት፣ እንዲሁም በሠራተኞች የስራ ክንውን ወይም የስነምግባር ሁኔታዎች ላይ በመመርኮዝ ሊገድብ ይችላል።

(4) በዚህ ክፍል በተገለፁት ትምህርት ቤቶች የማይሰሩ የ MCPS ሰራተኞች በዚህ ፖሊሲ እና የተዛማጅ ህጎችን መስፈርቶች መሰረት በማድረግ ለልጆቻቸው ለ COSAs ማመልከት ይችላሉ።

2. COSAs የሚከተሉትን ሂደቶች ማሟላት ይኖርባቸዋል፡-

a) የ COSA ማመልከቻዎች ዝውውሩ ከሚፈለግበት የትምህርት አመት አስቀድሞ ፌብሩዋሪ የመጀመሪያዉ የትምህርት ቀን እና ኤፕሪል የመጀመሪያዉ የትምህርት ቀን መካከል መቅረብ አለባቸው። የ COSA ጥያቄያቸውን የሚመለከት ውሳኔ ለወላጆች/ለአሳዳጊዎች እና ተማሪዎች

ከሜይ 31 በፊት ለማስታወቅ በተቻለ መጠን ጥረት ይደረጋል።ኤፕሪል ከመጀመሪያው የትምህርት ቀን በኋላ የሚቀርብ COSA ጥያቄ ተማሪው(ዋ) በሞንትጎመሪ ካውንቲ በአዲስ ነዋሪነት የመጣ(ች) ካልሆነ በስተቀር፣ ወይም ከኤፕሪል የመጀመሪያው የትምህርት ቀን አስቀድሞ ሊታሰብ የማይቻል አሳማኝ የሆነ ድንገተኛ ሁኔታ ኢጋጥሞ ካልሆነ በስተቀር ተቀባይነት አይኖረውም። ይህን ሁኔታ የሚደግፍ ሰነድ መቅረብ አለበት።

b) ከራሳቸዉ መጋቢ ት/ቤት ዉጪ የተፈቀደ COSA የሚያገኙ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በአትሌቲክስ ለመሳተፍ ብቁ ለመሆን በአዲሱ ትምህርት ቤት ለአንድ የካላንደር አመት መማር አለባቸው። ለዚህ ገደብ ማስወገጃ መጠየቅ ይቻላል።

c) COSA የሚቀበሉ ወላጆች/አሳዳጊዎች የማጓጓዝ ሃላፊነት ይኖርባቸዋል፣ እናም ለተማሪዎች የመኪና ማቆሚያ ደንብ እንደየ ት/ቤቱ እንደሚለያይ ማወቅ ይኖርባቸዋል።

d) የሎተሪ ምደባዎች ከተከናወኑ በኋላ በልዩ ችግር ምክንያት ከአንድ ኮንሰርሽም ት/ቤት ወደ ሌላ ኮንሰርሽም ት/ቤት ዝውውሮች የሚከናወኑት በኮንሶርሻ ምርጫና ትግበራ ፕሮግራም አገልግሎቶች ክፍል አማካይነት ነው።

e) የ COSA ማመልከቻ ከተመረመረ በኋላ ይጸድቃል ወይም ውድቅ ይደረጋል –

(1) ጥያቄው የቀረበበት ምክንያት (ምክንያቶች)፡-

(2) የልዩ ትምህርት (ስፔሻል ኢጁኬሽን) አገልግሎት ለሚያገኙ ተማሪዎች በተጠየቀው ትምህርት ቤት IEP መተግበር የሚቻል ከሆነ፥

(3) በተጠየቀው ትምህርት ቤት ውስጥ ሙያው የሚመለከታቸው ሰራተኞችና አገልግሎቶች የሚገኙ ከሆነ፥

(4) የትምህርት ቤት የመያዝ አቅም፣ የክፍል ደረጃ እና የክለስተር የመቀበል አቅምን ጨምሮ አዳዲስ ተማሪዎችን ለመቀበል የት/ቤቱን አቅምና ብቃት የሚያመለክቱ ሌሎች ጉዳዮች፤ እና

(5) የተጠየቀው ትምህርት ቤት የአጠቃቀም ደረጃ ከ 80 በመቶ በታች ከሆነ፣ በክፍል ወይም በክለስተር ደረጃ ማንኛውም የአቅም ብቃት ጉዳዮች ከተተነተነ/ምክንያታዊ ከሆነ በኋላ ጥያቄው ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይችላል።

3. በ COSA ኤሌመንተሪ ትምህርት ቤት እየተከታተሉ ያሉ ተማሪዎች ከአካባቢያቸው ት/ቤት ይልቅ በ COSA ሚድል ስኩል ለመማር እንደገና ማመልከት አለባቸው። በ2021-2022 የትምህርት ዓመት 6ኛ ክፍል ከሚገቡ ተማሪዎች ጀምሮ፣ የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት በ COSA የሚማር/የምትማር ተማሪ በዚያው መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት መጋቢ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መከታተል የሚፈልግ-የምትፈልግ ከሆነ ለ COSA እንደገና ማመልከት አለበ(ባ)ት። በ 2021-2022 3ኛክፍል ከሚገቡ ተማሪዎች ጀምሮ፣ በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ኢመርሽን ፕሮግራም ዉስጥ ያሉ ተማሪዎች ከአካባቢያቸዉ ት/ቤት ሌላ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ለመከታተል፣ በዚያው መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት መጋቢ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤትን ጨምሮ ለመከታተል ለ COSA ማመልከት አለባቸዉ።

4. በካውንቲ አቀፍ ፕሮግራሞች፣ በሪጅናል ፕሮግራሞች፣ ወይም በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደት ልዩ ግምት የተሰጣቸውና ሚዛናዊ ተደራሽነትን በስፋት ለማስፈን በየዓመቱ ተዘጋጅቶ በሚሠራጨዉ ዝርዝር ውስጥ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች እንዲከታተሉ ተቀባይነት አግኝተው የተመደቡ ተማሪዎች

በየአካባቢያቸው ት/ቤቶች ከሚከታተሉ በስተቀር በ COSA ትምህርት ቤት አይመደቡም። በፕሮግራሙ መሳተፍ ካቋረጡ በኋላ ተማሪዎችን ወደ አካባቢያቸው ት/ቤት እንዲመለሱ ለማድረግ የMCPS መብቱ የተጠበቀ ነው።

5. MCPS ከዚህ በታች እንደተገለፀው አንዳንድ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የአካዳሚያዊ ዝውውር ጥያቄን ምላሽ ከመስጠት አኳያ አንዳንድ ጥያቄዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት በዚህ ፖሊሲ ላይ ከተገለጸው የ COSA አሠራር የተለየ ሒደት ሊተገበር ይችላል።

   a) ተማሪዎች ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት በአንዱ ለመሳተፍ አካደሚያዊ የዝውውር ጥያቄ ሊያቀርቡ ይችላሉ –

      (1) በዲስትሪክት ወይም በትምህርት ቤት የኮርስ መግለጫ ካታሎግ ውስጥ እንደተገለጸው፣ በተማሪው(ዋ) የአካባቢ ትምህርት ቤት የማይገኙ ዓመታት የሚፈጁ ተከታታይነት ያላቸው በርካታ ተዛማጅ ኮርሶች፣ ወይም

      (2) ብዙ ዓመት የሚፈጅ አንድ ኮርስ፣ በዲስትሪክት ወይም በትምህርት ቤት ኮርስ መግለጫ-ካታሎግ ላይ እንደተገለጸው፣ በተማሪው(ዋ) የአካባቢ ትምህርት ቤት የማይገኝ ከሆነ።

   b) እንዲህ ዓይነቱ ሂደት ለኮርስ ምዝገባ ከ MCPS የጊዜ ሰሌዳዎች እና ከሠራተኛ ፍላጎቶች ጋር የሚጣጣም የአካዴሚክ ዝዉዉር ጥያቄዎችን የማስገቢያ የጊዜ ገደቦችን ያካትታል።

   c) እንዲህ ዓይነቶቹ ዝዉዉሮች የሚፈቀዱት የአካባቢ ተማሪዎች ከተመዘገቡ በኋላ ቦታ ከተገኘ ብቻ ነዉ።

   d) ከዲስትሪክቱ ስትራቴጂያዊ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች ጋር በሚጣጣም መልኩ፣ የአካዴሚያዊ ሽግግር ጥያቄውን ከመፍቀድ ይልቅ፣ MCPS በተማሪው(ዋ) የአካባቢ ት/ቤት በአካዴሚያዊ መርሃግብሮች ላይ ማስተካከያዎችን ማድረግንም ግንዛቤ ዉስጥ ሊያስገባ ይችላል።

   e) የአካዴሚያዊ ዝዉዉር ጥያቄው ከተፈቀደላቸው የኮርስ ቅደም ተከተል ከለቀቁ፥ ተማሪዎች ወደ አካባቢያቸው ት/ቤት እንዲመለሱ ለማድረግ MCPS መብቱ የተጠበቀ ነው።

6. ማንም ልጅ በወቅቱ ታላቅ ወንድም/እህት በቋንቋ ኢመርዥን ፕሮግራም እየተማረ(ች) ከሆነ፣ እና ታናሹ ለመመዝገብ በሚፈልግበት-በምትፈልግበት ዓመት በቋንቋ ኢመርዥን ፕሮግራም የሚቀጥል-የምትቀጥል ከሆነ፣ ወደ ቋንቋ ኢመርዥን ፕሮግራም ለመግባት በሱፐርኢንተንደንቱ አማካይነት በተመሠረተ የሎተሪ ሂደት ይሳተፋል/ትሳተፋለች። የዚህ አይነቱ ሎተሪ እነዚህን እሳቤዎች የያዘ የመመዘኛ ሂደት ያጠቃልላል፦ (ሀ) በአሁኑ ወቅት በቋንቋ ኢመርሽን ፕሮግራም የተመዘገበ(ች) እና ታናሽ ወንድም/እህት ለመመዝገብ በሚ(ምት)ፈልግበት አመት በዚያው የቋንቋ ኢመርሽን ፕሮግራም በመመዝገብ የሚ(ምት)ቀጥል ታላቅ ወንድም/እህት ያላቸው ተማሪዎች፤ (ለ) ማህበራዊ-ኤኮኖሚያዊ ይዘት እና ድህነት፤ እንዲሁም (ሐ) በተለዩ ሁኔታዎች አካባቢን የሚሸፍንና የመሳሰሉት በት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ሌሎች ታሳቢ የሚደረጉ ነገሮች። በ 2017-2018 የትምህርት ዓመት በቋንቋ ኢመርሽን ፕሮግራም የተመዘገበ(ች) ታናሽ ወንድም/እህት ለመመዝገብ በሚ(ምት)ፈልግበት አመት በዚያው የቋንቋ ኢመርሽን ፕሮግራም በመመዝገብ የሚ(ምት)ቀጥል ታላቅ ወንድም/እህት ያለው/ያላት ማንኛው(ዋ)ም ልጅ፣ በዚያ ፕሮግራም ውስጥ ለመግባት በሚካሄደው ሎተሪ መሳተፍ ሳያስፈልግ በቋንቋ ኢመርሽኑ ፕሮግራም መመዝገብ ይችላል/ትላለች።

D. **የሚፈለጉ ውጤቶች**

1. ለእያንዳንዱ ትምህርት ቤት በአካባቢ ትምህርት ቤት የመማርን እና የቦታ ፍላጎቶችን በማመቻቸት ወይም እጥረት የታየባቸውን ጉዳዮች እና የሠራተኛ ምደባ የመሳሰሉትን በማስተካከል የትምህርት ቤት ማካለልን በተረጋጋ ሁኔታ ለመጠበቅ

2. ተማሪዎች በሠነድ ማስረጃ ሊረጋገጥ የሚችል ከባድ ሁኔታ በሚያጋጥማቸው ወቅት፣ ቤተሰብ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ ቦታ ሲቀይሩ፣ ወይም ወንድም/እህት በሚማርበት-በምትማርበት ተመሣሳይ ት/ቤት ለመግባት የሚያስገድዱ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ COSA እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ የአሠራር ሒደቱን ለማሳወቅ

3. የ COSA አሠራር ሂደት በካውንቲ አቀፍ ደረጃ ከሚካሄዱ የፕሮግራሞች ምዝገባ አሠራር፣ የአካዳሚያዊ ዝውውር ጥያቄዎች፣ እና በ MCPS ሠራተኛ አነሳሽነት የሚከናወኑ አስተዳደራዊ ምደባዎች ይልቅ በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት በአስተዳደራዊ ደምብ በተሰጡ መመዘኛዎች መሠረት ልዩነቱን ግልጽ ለማድረግ

E. **ተግባራዊ ስልቶች**

ይህ ፖሊሲ ተግባራዊ የሚሆነው አስተዳደራዊ ደንብን በመከተል ነው።

F. **ግምገማ እና ሪፖርት**

ይህ ፖሊሲ በትምህርት ቦርድ የፖሊሲ ክለሳ ሂደት መሰረት በየዓመቱ የሚከለስ-የሚገመገም ይሆናል።

**የፖሊሲው ታሪክ፡-** የውሳኔ ቁ. 288-72፣ ኤፕረል 11/1972፣ የተሻሻለው በውሳኔ ቁ. 825-72፣ ዲሰምበር 12/1972 ዳግመኛ የተሻሻለ ቅርፅ ያገኘው በውሳኔ ቁ. 333-86 ጁን 12/1986 እና ውሳኔ ቁ. 458-86 ኦገስት 12/1986 የፀደቀው በውሳኔ ቁ. 517-86፣ ሴፕተምበር 22/1986 የተገመገመው ፌብሩወሪ፣ 1995 የተሻሻለው በውሳኔ ቁ. 92-02፣ ማርች 12/2002 መጠነኛ ማሻሻያ ተደርጎበታል፣ ኖቨምበር 16/2006 የተሻሻለው በውሳኔ ቁ. 124-17፥ ማርች 17/2017 በውሳኔ ቁጥር. 457-20 ተሻሽሏል፥ እና በውሳኔ ቁጥር 458-20 ኦክቶበር 6/2020 ተሻሽሏል።